# በልጆች ላይ የሚከሰት አልፎ አልፎ የሚያጋጥም የ ኮቪድ 19 ምልክቶች

በኮቭድ-19 (COVID-19) የታመሙ አብዛኞቹ ልጆች መለስተኛ ምልክቶች ይታዩባቸዋል። ሆኖም አንዳንድ ህጻናት እንዲሁም ወጣቶች በኮቪድ 19 ምክንያት ያልተለመዱ እንዲሁም የተወሳሰበ የጤና እክል ያጋጥማቸዋል። በዚህ ምክንያት የሚያጋጥማቸው የጤና እክል መልታይ ሲስተም ኢንፍላማቶሪ ሲንድሮም ኢን ችልድረን ይባላል። ይህ የጤና እክል ያጋጠማቸው ልጆችም ሆኑ ወጣቶች ወደ ሆስፒታል በመሄድ ህክምና ሊከታተሉ ይገባቸዋል። መልታይ ሲስተም ኢንፍላማቶሪ ሲንድሮም ኢን ችልድረን በተሰኘው በሽታ የተጠቁ ልጆች ሁሉ የኮቪድ 19 ምልክት አላቸው ማለት ግን አይደለም ። አንዳንዶቹ ምልክቱ ከሳምንታት በፊት ታይቶባቸው ሊሆን ይችላል።

አልፎ አልፎ የሚያጋጥም ቢሆንም ወላጆች ሆኑ የልጆች ጠባቂወች የሚከተሉትን ምልክቶች በልጆች ላይ አለመኖራቸውን አረጋግጡ።

- ከ24 ሰዓታት በላይ የቆየ ተከታታይ ትኩሳት
- ከመጠን ያለፈ የድካም ስሜት
- የሆድ ህመም
- ተቅማጥ
- ማቅለሽልሽ
- ሰውነት ላይ የሚወጣ ሽፍታ
- የአይን ቅላት
- የአንገት ህመም

ከላይ የተዘረዘሩትን ምልክቶች በልጆች ላይ ካስተዋሉ ባፋጣኝ ወደ ዶክተር ይውሰዱዋቸው።

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የከፉ ምልክቶች በልጆች ላይ ካዩ ወዲያውኑ ወደ አጣዳፊ ህክምና ይውሰዱዋቸው።

- የመትንፈስ ችግር (የትንፋሽ እጥረት)
- በደረት ላይ የሚከሰት ህመም
- የፊት ግርጣት
- ከባድ የሆድ ህመም
- ግራ መጋባት
- ነቅቶ መቆየት ወይንም መንቃት አለመቻል

በተመጣጣኝ ዋጋ የጥርስ፣ ዶክተር ወይንም ነርስ ና ጥራት ያለዉ የጤና እንክብካቤ ለማግኘት ዶክተር ከሌሎት **ኮሚኒቲ ሔልዝ አክሰስ ፕሮግራም** (ድህረ ገጽ በእንግልዝኛ) የሚባለውን ያግኙ። አገልግሎቱ ነጻ ነዉ አስተርጓሚዎችም አሉ።

- ስልክ :-1-800-756-5437
- ኢሚል :-CHAP@kingcounty.gov
- ድሕረ ገጽ:-www.kingcounty.gov/CHAP (ድህረ ገጽ በእንግልዝኛ)

ወደ ስፓኒሽ፣ ኮሪያን፣ ቬትናምኛ ና ቻይንኛ የተተረጎሙትን መረጃዎች ጨምሮ ከሲዲሲ የበለጠ ይማሩ።



Public Health
Seattle & King County